የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራ ስምንተኛ ዓመት ቁጥር ፷፪
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

18th Year No. 62
ADDIS ABABA 4th September, 2012

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፰/፪ሺ፬ ዓ.ም

**የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ……… …..ገጽ ፮ሺ፭፻፶፭**

CONTENTS

**Proclamation No. 768/2012**

**Export Trade Duty Incentive Schemes Proclamation ……. Page 6555**

**አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፰/፪ሺ፬**

**ስለወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት የወጣ አዋጅ**

የአገሪቱን የኢንዱስትሪ እድገት በማፋጠን የኢኮኖሚ ልማትን ማረጋገጥ እና ለልማትና ኢንቨስትመንት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ማጎልበት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ወደ ኢንዱስትሪ መር ኢኮኖሚ ለመሸጋገር እንዲቻል እሴት መጨመር የሚያስችል የምርት ሂደት ሰንሰለትን የሚያጠናክር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ በወጪ ንግድ ሥራ ላይ የሚሰማሩትን ባለሀብቶች የሚያበረታቱ አዳዲስ ሥርዓቶችን በመዘርጋት እንዲሁም ነባሮቹን በማሻሻል የአገሪቱን ምርቶች በዓለም አቀፍ የንግድ ልውውጥ ውስጥ ብቁና ተወዳዳሪ መሆን የሚችሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር ፯፻፷፰/፪ሺ፬" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**PROCLAMATION No. 768/2012.**

**A PROCLAMATION ON EXPORT TRADE DUTY INCENTIVE SCHEMES**

WHEREAS, it is necessary to ensure economic development by accelerating industrial growth of the country and to improve the foreign exchange earning needed for development and investment;

WHEREAS, to achieve transformation into industry led economy, it is necessary to establish a system of reinforcing value creation in the process of production;

WHEREAS, it is essential to create conducive environment for domestic products to become competitive in international commodity markets by rendering efficient the scheme of incentives available for export trade through rectification of deficiencies noticeable in the scheme and by introducing new incentives having direct or indirect impact of motivating investors engaged in export trade ;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (11) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## PART ONE

## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Export Trade Duty Incentive Schemes Proclamation No768/2012".

## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ “ተመላሽ ቀረጥ” ማለት ወደ ውጭ ለሚላኩ ሸቀጦች ማምረቻ በሚውሉ ጥሬ ዕቃዎች እና አላቂ የምርት መገልገያዎች ላይ የተከፈለ እና ሸቀጡ ተመርቶ ወደ ውጭ በሚላክበት ጊዜ ለከፋዩ ተመላሽ የሚደረግ ቀረጥ ነው፤

፪/ “ቀረጥ” ማለት ወደ አገር ውስጥ በሚገቡ ወይም በአገር ውስጥ በሚመረቱ ጥሬ ዕቃዎች፣ ሸቀጦች ወይም አላቂ የምርት መገልገያዎች ላይ የሚከፈል ቀጥተኛ ያልሆነ ማንኛውም ታክስ ወይም ቀረጥ ነው፤

፫/ “ወደ ውጭ መላክ” ማለት ከኢትዮጵያ ውጭ ሸቀጦችን መላክ ሲሆን ከኢትዮጵያ ውጭ ለመሄድ በተዘጋጁ ማጓጓዣዎች ላይ ሸቀጦችን መጫንን ይጨምራል፤

፬/ “ሸቀጥ” ማለት ወደ አገር በገባበት ሁኔታ ተመልሶ የተላከ ወይም ለውጭ ገበያ እንዲውል የተመረተ ዕቃ ሲሆን ወደ ውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ለመያዣ፣ ለመጠቅለያ ወይም ለማሸጊያ የሚውለውን ይጨምራል፤

፭/ “ጥሬ ዕቃ” ማለት በማምረት ወይም በመሥራት ሂደት ውስጥ ተደባልቆ ወይም ተገጣጥሞ ለውጭ ገበያ የሚውል ሸቀጥ ለማምረት የሚውል ዕቃ ሲሆን ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦችን ለመያዣ፣ ለመጠቅለያ ወይም ለማሸጊያ የሚውለውን ይጨምራል፤

፮/ “አላቂ የምርት መገልገያ" ማለት በምርት ሂደት ውስጥ ጥቅም ላይ ከዋለ በኋላ ወይም በምርት ዓይነት ለውጥ ምክንያት ከአገልግሎት ውጪ የሚሆን ዕቃ ሲሆን ምርቱን ሙሉ ለሙሉ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የተቋቋመ አምራች በቀጥታ በማምረት ተግባር ላይ እንዲውሉ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገባቸውን ዘይቶች፣ ቅባቶችና ሌሎች ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገሮችን ይጨምራል፤

፯/ “ዕቃ” ማለት ማንኛውም ተንቀሳቃሽ ንብረት ሲሆን ጥሬ ዕቃን፣ አላቂ የምርት መገልገያን እና ሸቀጥን ይጨምራል፤

፰/ “ላኪ” ማለት በአገር ውስጥ የተመረቱ ሸቀጦችን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የንግድ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ነው፤

፱/ “አምራች” ማለት አምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ነው፤

፲/ “አምራች ላኪ” ማለት ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

## 2. Definitions

In this Proclamation unless the context otherwise requires :

1/ “duty draw-back” means duty paid on raw materials and accessories used in the production of commodities and refunded to the payer upon exportation of the commodity processed;

2/ “duty” means any indirect tax or duty payable on raw materials and commodities or accessories imported or produced locally;

3/ “export” means sending commodities to a place outside Ethiopia, and includes the loading on same on a carrier proceeding to a foreign port;

4/ “commodity “ means goods re-exported in the same condition or goods produced for foreign market and includes goods used for containing, wrapping or packing export commodities;

5/ “raw material” means goods that are mixed with or fixed to other goods in the production process to bring about commodities for export, and includes goods to be used for containing, wrapping or packing export commodities;

6/ “accessory” means goods which become out of service as a result of being used in the process of production or because of change in the type of product of a manufacturer, and includes imported oil, lubricants, and other energy generating substance used by a producer which is wholly engaged in manufacturing commodities for export;

7/ “goods” means any movable property including raw materials, accessories and commodities;

8/ “exporter” means a person licensed to engage in supplying locally produced commodities to foreign market;

9/ “producer” means producer exporter or indirect producer exporter;

10/ “producer exporter” means a person engaged in producing commodity and supplying same in whole ,in part or periodically to foreign market;

፲፩/ “ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ” ማለት ያመረተውን ምርት በጥሬ ዕቃ ወይም በከፊል በተፈበረከ ወይም ባለቀለት ዕቃ መልኩ ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለሌላ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ፣ ለአምራች ላኪ ወይም ለላኪ የሚያቀርብ ሰው ነው፤

፲፪/ “ጥሬ ዕቃ አቅራቢ” ማለት ከውጭ ያመጣውን ጥሬ ዕቃ በምርት ሂደት ውስጥ እንዲያልፍ ሳያደርግ ባለበት ሁኔታ ሙሉ በሙሉ፣ በከፊል ወይም በተወሰነ ወቅት ለአምራች ላኪ ወይም ቀጥተኛ ላልሆነ አምራች ላኪ የሚያቀርብ ሰው ሲሆን የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነን ሰው አይጨምርም፤

፲፫/ “የቫውቸር ደብተር” ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ለውጭ ገበያ የሚውሉ ሸቀጦችን ለማምረት ወደ አገር በሚያስገባቸው ወይም ከቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን በሚገዛቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ የሚከፈለውን የቀረጥ ልክ ለመመዝገብ እንዲያገለግል በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚታተም ሰነድ ነው፤

፲፬/ “የግብዓት ምርት ጥምርታ” ማለት በተወሰነ መለኪያ አንድ የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ፍጆታ መጠን የሚያሳይ ነው፤

፲፭/ “የአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ተመላሽ ቀረጥ መጣኔ” ማለት አንድን የወጪ ምርት ለማምረት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ እና አላቂ የምርት መገልገያ አማካይ ፍጆታ በመለየት በእነዚህ ላይ የተከፈለውን ቀረጥ ምርቱ ለውጭ ገበያ ከቀረበበት የፎብ ዋጋ አንፃር በማስላት ተመላሽ የሚደረግበት የመቶኛ መጣኔ ነው፤

፲፮/ “ቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ” ማለት ለምርት አገልግሎት ከቀረጥ ነጻ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን በመጠቀም ያመረተውን ምርት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርብ በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቁጥጥር የሚደረግበት ፋብሪካ ነው፤

፲፯/ “ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን” ማለት ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ ለሚቀርብ ምርት ማምረቻ የሚውሉ ከቀረጥ ነጻ ሆነው የገቡ ጥሬ ዕቃዎችና በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች የተመረቱ ምርቶች የሚቀመጡበትና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና በፋብሪካው በጋራ ቁጥጥር የሚደረግበት መጋዘን ነው፤

፲፰/ “ቦንድድ የግብዓት አቅርቦት መጋዘን” ማለት ፈቃድ በተሰጠው አቅራቢ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ የገባ ጥሬ ዕቃ ወይም አላቂ የምርት መገልገያ ለአምራቾች እስከሚሸጥ ድረስ የሚቀመጥበት በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣንና በአቅራቢው ቁጥጥር የሚደረግበት መጋዘን ነው፤

11/ “indirect producer exporter” means a person supplying its products in whole, in part or periodically to another indirect producer exporter, producer exporter or exporter in the form of raw material, semi-processed good or finished good;

12/ “raw material supplier” means a person supplying raw material in whole, in part or periodically to a producer exporter or indirect producer exporter without processing it, but does not include a person who is beneficiary of the bonded input supplies warehouse scheme ;

13/ “voucher book” means a document printed by the Ethiopian Revenues and Customs Authority, to be used for recording the balance of duty payable on raw materials imported or bought from bonded input supplies warehouse, for use in the production of goods for external market by persons availing themselves of the voucher scheme under this Proclamation;

14/ “input output coefficient” means a specified measurement for the use of raw material or accessory to produce one unit of export goods;

15/ “all industry rate” means the rate of duty draw-back on export goods calculated as percentage of their FOB value on the basis of the average requirement of raw materials and accessories to produce such goods;

16/ “bonded export factory” means a factory under the control of the Ethiopian Revenues and Customs Authority which produces goods exclusively for export using raw materials imported free of duty ;

17/ “bonded export manufacturing warehouse” means a warehouse under joint control of the Ethiopian Revenus and Customs Authority and the factory concerned, where raw materials imported free of duty for use in the production of goods destined exclusively for export as well as goods produced using such raw materials are stored;

18/ “bonded input supplies warehouse” means a warehouse under the joint control of the Ethiopian Revenues and Customs Authority and the supplier concerned, where raw materials and accessories imported free of duty by a licensed supplier are stored until such time as they are sold to producers;

፲፱/ "የኢንዱስትሪ ቀጠና" ማለት ማናቸውም የተቀናጀ መሠረተ ልማት የተሟላለትና የፖሊሲ ማበረታቻዎች ያሉት ለኢንዱስትሪ የተከለለ ቦታ ነው፤

፳/ "ቀጥተኛ ላኪ" ማለት አምራች ላኪ ወይም ላኪ ነው፤

፳፩/ "ቀጥተኛ ያልሆነ ላኪ" ማለት ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ወይም ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ነው፤

፳፪/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፳፫/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል፡፡

## ፫. የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች

፩/ የሚከተሉት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓቶች በዚህ አዋጅ ተቋቁመዋል፡-

ሀ) የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት፤

ለ) የቫውቸር ሥርዓት፤

ሐ) የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት፤

መ) የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት፤

ሠ) የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት፤ እና

ረ) የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት፡፡

፪/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ በማውጣት ተጨማሪ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት በሥራ ላይ እንዲውል ሊፈቅድ ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የተመላሽ ቀረጥ ስርዓት

## ፬. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

የተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

፩/ አምራች ላኪዎች፤

፪/ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፤

፫/ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች፤ እና

፬/ ላኪዎች፡፡

## ፭. ቀረጥን ተመላሽ ስለማድረግ

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፬ የተመለከቱት የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ከውጭ በሚያስመጧቸው ወይም በአገር ውስጥ በሚገዟቸው ዕቃዎች ላይ የተከፈለው ቀረጥ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተሟልተው ሲገኙ ተመላሽ ይደረግላቸዋል፡፡

19/ "industrial zone" means an area set aside for industry which is equipped with the necessary infrastructural facilities and enjoys policy incentives;

20/ "direct exporter" means exporter producer or exporter;

21/ "indirect exporter" means indirect producer exporter or raw material supplier;

22/ "person" means natural or juridical person;

23/ any expression in the masculine gender includes the feminine.

## 3. The Duty Incentive Schemes

1/ The following duty incentive schemes are hereby established:

a) the duty draw-back scheme;

b) the voucher scheme;

c) the bonded export factory scheme;

d) the bonded manufacturing warehouse scheme;

e) the bonded input supplies warehouse scheme; and

f) the industrial zone scheme.

2/ Where necessary, the Council of Ministers may, by regulation, authorize the application of other duty incentive schemes.

## PART TWO

## DUTY DRAW-BACK SCHEME

## 4. Beneficiaries of the Scheme

The following shall be eligible for duty draw-back scheme:

1/ producer exporters;

2/ indirect producer exporters;

3/ raw material suppliers;

4/ exporters.

## 5. Duty Draw-Back

1/ Duty paid on goods imported or purchased locally by beneficiaries of the scheme listed in Article 4 of this Proclamation shall be refunded to them upon fulfillment of conditions laid down in directive to be issued by the Ministry of Finance and Economic Development.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የተከፈለው ቀረጥ ልክ ከብር ፩ሺ በታች ከሆነ ተመላሽ አይደረግም።

፫/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን በዚህ አዋጅ መሠረት ተመላሽ ሊደረግ የሚገባውን ገንዘብ የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄው ተሟልቶ በቀረበለት በ፴ ቀናት ውስጥ ለመብቱ ተጠቃሚ ተመላሽ ያደርጋል።

፬/ ለተመላሽ ቀረጥ የሚውለው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

## ፮. <u>የተመላሽ ቀረጥ ልክ</u>

፩/ የወጪ ምርት ለማምረት በጥቅም ላይ የዋሉ ጥሬ ዕቃዎችንና አላቂ የምርት መገልገያዎችን በሚመለከት ተመላሽ የሚደረገው ቀረጥ መጠን በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የተመላሽ ቀረጥ መጣኔ መሰረት የሚሰላ ይሆናል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው የአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የተመላሽ ቀረጥ መጣኔ በሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ ተመላሽ የሚደረገው ቀረጥ መጠን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪(፪) መሠረት በሚወሰነው የግብዓት ምርት ጥመርታ ላይ ተመሥርቶ ይሰላል።

## ፯. <u>የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ አቀራረብ</u>

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተመላሽ ቀረጥ ጥያቄ አቀራረብንና ተያይዘው መቅረብ የሚገባቸውን ማስረጃዎች የሚመለከት መመሪያ ያወጣል።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የቫውቸር ሥርዓት</u>

## ፰. <u>የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች</u>

የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚችሉት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የሚሰጣቸው የሚከተሉት ሰዎች ይሆናሉ፡ -

፩/ አምራች ላኪዎች፤

፪/ ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች፤ እና

፫/ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች።

## ፱. <u>የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን መሟላት የሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

፩/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር በቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚችሉ የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች ማሟላት የሚገባቸውን ቅድመ ሁኔታዎች የሚወስን መመሪያ ያወጣል።

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, duty paid may not be refunded where the amount is less than Birr 1,000.

3/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall effect payment in accordance with this Proclamation to the beneficiaries concerned within 30 days of receipt of complete claim for duty draw-back.

4/ The budget required for duty draw-back shall be allocated by the government.

## 6. <u>Duty Draw-Back Rate</u>

1/ The amount of duty draw-back with respect to raw materials and accessories used in the process of production of export commodities shall be calculated in accordance with all industry rates of duty draw-back

2/ Pending the implementation of all industry rates of duty draw-back referred to in sub-article (1) of this Article, amount of the duty draw-back shall be calculated on the basis of input and output coefficient determined pursuant to Article 22(2) of this Proclamation.

## 7. <u>Claims for Duty Draw-Back</u>

The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall issue directive prescribing the manner in which claims for duty draw-back may be filed and the supporting evidence to be presented along with duty draw-back claims.

## <u>PART THREE</u>

## <u>VOUCHER SCHEME</u>

## 8. <u>Beneficiaries of the Scheme</u>

Beneficiaries of the voucher scheme shall be the following persons who have obtained eligibility certificate issued by the Ministry of Industry:

1/ producer exporters;

2/ indirect producer exporters; and

3/ raw material suppliers.

## 9. <u>Conditions to be Fulfilled to Become Beneficiary of the Voucher Scheme</u>

1/ The Ministry of Industry shall issue directive specifiying the conditions to be fulfilled to be eligible for the voucher scheme.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም የሥርዓቱ ተጠቃሚ ጥሬ ዕቃዎችን አቅራቢዎች በሚሰጡት ዱቤ ወይም በፍራንኮ ቫሉታ ወደ አገር የሚያስገባ ከሆነ፦

ሀ) ተፈላጊው ምርት በአገር ውስጥ ከተመረተ በኋላ የምርቱ ተቀባይ መኖሩን የሚያረጋግጥ ከገዢው የተላከ ትዕዛዝ ወይም ከገዢው ጋር የተደረገ ውል ማቅረብ የሚችል፤ ወይም

ለ) ጥሬ ዕቃው የወጪ ምርቶችን ለማምረት ውጭ አገር ከሚገኝ ተባባሪ ኩባንያ የተላከለት መሆኑን የሚገልጽ ማስረጃ ማቅረብ የሚችል፤

መሆን አለበት፡፡

## ፲. የቫውቸር ሥርዓት አፈፃፀም

፩/ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው ሰዎች በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የቫውቸር ደብተር ይሰጣቸዋል፡፡

፪/ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ አገር በሚያስገቡት ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥና ታክስ በቫውቸር ደብተሩ ላይ ተመዝግቦ ዕቃውን እንዲረከቡ ይደረጋል፡፡

፫/ በቫውቸር ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ ለተጠቃሚው ከደረሰበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መላክ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ ፶ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፮/ ጥሬ ዕቃ አቅራቢዎች በቫውቸር ሥርዓት ተጠቅመው ዕቃዎችን ወደአገር ማስገባት የሚችሉት በሚያስገቡት ዕቃ ላይ ሊከፈል ከሚገባው ቀረጥና ታክስ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የኢንሹራንስ ቦንድ ሲያቀርቡ ይሆናል፡፡

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article a beneficiary of the scheme shall, if he imports raw materials on suppliers credit or franco-valuta, be required to submit evidence confirming that:

a) the commodity has demand and that the demand is confirmed by a purchase order issued by the prospective buyer or submit a purchase agreement concluded with the prospective buyer; or

b) the raw materials are sent by affiliate foreign company with the objective of producing export commodities.

## 10. Procedure for the Application of Voucher Scheme

1/ Persons who have obtained certificate of eligibility from the Ministry of Industry shall be granted voucher book by the Ethiopian Revenues and Customs Authority.

2/ Beneficiaries of the voucher scheme shall be entitled to take delivery of goods they import, upon the entry in the voucher book of the amount of duty payable on such goods.

3/ Raw materials imported under the voucher scheme shall be used in the production of export commodity and the commodity so produced shall be exported within one year from receipt of such raw materials by the beneficiary; provided, however, that the Ethiopian Revenues and Customs Authority may extend this period by one additional year taking into consideration the nature of the raw materials.

4/ A beneficiary of the voucher scheme desiring extension of the period stipulated in sub-article (3) of this Article shall be required to submit his application for extension one month before the expiry of such period.

5/ A beneficiary of the voucher scheme who has not secured permission for extension of the period stipulated under sub-article (3) of this Article, or to sell raw materials imported under this scheme upon payment of duty chargeable on such raw materials in accordance with Article 25 of this Proclamation shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw material, be required to pay 50% of the duty.

6/ Raw material suppliers may import goods under the voucher scheme if they furnish guarantee in the form of insurance bond in an amount equal to the amount of duty payable on the goods to be imported.

፯/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቫውቸር ስርዓት የጉምሩክ ሥርዓት አፈፃፀምን፣ የቫውቸር ደብተር ይዘትን እና የቫውቸር ደብተር ጥያቄ አቀራረብን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል፡፡

**ክፍል አራት**

**የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት**

## ፲፩. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

፩/ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ መሆን የሚችሉት፡ -

ሀ) ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ፤

ለ) በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው፤ እና

ሐ) የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ የማምረቻ ፋብሪካ ያላቸው፤

ሰዎች ይሆናሉ፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገባቸው መስፈርቶችን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጠቃሚዎቹ የማምረቻ ፋብሪካዎች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ፡፡

## ፲፪. የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት አፈፃፀም

፩/ የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባው ጥሬ ዕቃ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ወደ ፋብሪካው ይጓጓዛል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ የሚገባውን ጥሬ ዕቃ እና ከፋብሪካው ለውጭ ገበያ የሚላከውን ምርት ይቆጣጠራል፡፡

፫/ በቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ ወደ ፋብሪካው ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መላክ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

7/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall issue directive concerning the customs procedure applicable to the voucher scheme, the content of voucher book and the manner of filing application for voucher book.

**SECTION FOUR**

**BONDED EXPORT FACTORY SCHEME**

## 11. Beneficiaries of the Scheme

1/ Beneficiaries of the bonded export factory scheme shall be persons who have:

a) engaged exclusively in the production of export commodities;

b) obtained certificate of eligibility from the Ministry of Industry; and

c) a manufacturing plant which meets the standards set by the Ethiopian Revenues and Customs Authority.

2/ The Ministry of Industry shall issue directive stipulating the criteria to be fulfilled to obtain certificate of eligibility to become beneficiary of the scheme, and the Ethiopian Revenues and Customs Authority shall issue directive defining the standards to be met by the manufacturing plants owned by beneficiaries of the scheme.

## 12. Procedure for the Application of Bonded Export Factory Scheme

1/ Raw materials imported by a person who is beneficiary of the bonded export factory scheme shall be transported to the factory under the control of customs without being subject to payment of duty.

2/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall inspect raw materials brought into the bonded export factory and goods exported from the factory.

3/ Raw materials imported under the bonded export factory scheme shall be used in the production of export commodity and the commodity so produced shall be exported within one year from receipt of such raw materials by the factory; provided, however, that the Ethiopian Revenues and Customs Authority may extend this period by one additional year taking into consideration the nature of the raw materials.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ ማንኛውም የሥርዓቱ ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የመጠቀሚያው የጊዜ ገደብ እንዲራዘም ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሠረት ቀረጥና ታክሱን ከፍሎ በአገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን ሂሳብ ፶ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፮/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቦንድድ ኤክስፖርት ፋብሪካ ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያበቁ ተጨማሪ መስፈርቶችን፣ የድህረ ዕቃ አወጣጥ ኦዲት ሥርዓትን እና የሥርዓቱን አፈፃፀም የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል አምስት

## የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት

### ፲፫. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

፩/ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚዎች የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟሉ በኢንዱስትሪ ቀጠና ውስጥ የሚቋቋሙ ኢንዱስትሪዎች ይሆናሉ፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆንየሚችሉ ኢንዱስትሪዎች ሊያሟሉዋቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስን መመሪያ ያወጣል፡፡

### ፲፬. የሥርዓቱ አፈፃፀም

፩/ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባው ጥሬ ዕቃ ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከጉምሩክ ጣቢያዎች ወደ ኢንዱስትሪው ቀጠና ይጓጓዛል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ኢንዱስትሪ ቀጠና የሚገባውን ጥሬ ዕቃ እና በኢንዱስትሪ ቀጠናው ተመርቶ ለውጭ እና ለአገር ውስጥ ገበያ የሚቀርበውን ምርት ይቆጣጠራል፡፡

፫/ በኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ወደ አገር የገባ ጥሬ ዕቃ ወደ ኢንዱስትሪው ቀጠና ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ወይም ለአገር ውስጥ ገበያ መቅረብ አለበት፡፡

፬/ የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው፡ -

ሀ) ካመረተው ሸቀጥ ውስጥ ለውጭ ገበያ የሚቀርበውንና ለአገር ውስጥ ፍጆታ የሚውለውን ለይቶ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማሳወቅ፤ እና

4/ A beneficiary of the scheme desiring extension of the period stipulated in sub-article (3) of this Article shall submit his application one month before the expiry of such period.

5/ A beneficiary of the scheme who has not secured permission for extension of the period stipulated in sub article (3) of this Article, or to sell the raw materials imported under the scheme upon payment of duty chargeable on the raw materials in accordance with Article 25 of this Proclamation shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw materials, be required to pay 50% of the duty.

6/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority may issue directive prescribing additional conditions to be fulfilled to become beneficiary of the bonded export factory scheme, post delivery audit of goods and guidelines for the application of the scheme.

## PART FIVE

## THE INDUSTRIAL ZONE SCHEME

### 13. Beneficiaries of the Scheme

1/ Beneficiaries of the industrial zone scheme shall be industries setup within an industrial zone and which meet the criteria of eligibility set by the Ministry of Industry.

2/ The Ministry of Industry shall issue directive stipulating the criteria to be fulfilled by industries to become beneficiary of the industrial zone scheme.

### 14. Procedure for the Application of the Scheme

1/ Raw materials imported by a person who is beneficiary of the industrial zone scheme shall be transported from a customs post to the factory under the control of customs without being subject to payment of duty.

2/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall inspect raw materials brought into an industrial zone and goods produced by industries within the zone for export and local consumption.

3/ Raw materials imported under the industrial zone scheme must be put to use in the production of commodities for export or local consumption within one year of receipt of such raw materials by an industry within the zone.

4/ A person who is beneficiary of the industrial zone scheme shall:

a) assort its products by their destination and report same to the Ethiopian Revenues and Customs Authority; and

ለ) ለውጭ ገበያ እንዲውል ከኢንዱስትሪው ቀጠና የወጣው ምርት ለውጭ ገበያ መላኩን የሚያሳይ መረጃ ምርቱ ከኢንዱስትሪው ቀጠና በወጣ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ማቅረብ፤

አለበት፡፡

፭/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ተመላሽ ቀረጥ መጣኔን መሠረት በማድረግ በኢንዱስትሪ ቀጠና ተመርቶ ለአገር ውስጥ ገበያ በሚውለው ምርት ላይ ምርቱ ከኢንዱስትሪው መንደር ከመውጣቱ በፊት ቀረጥ ያስከፍላል፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ ማንኛውም የሥርዓቱ ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከመጠናቀቁ ከአንድ ወር በፊት ሲያመለክት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ የጊዜ ገደቡን ከአንድ ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝምለት ይችላል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፮) መሠረት የመጠቀሚያ የጊዜ ገደብ ያልተራዘመለት የኢንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን ፶ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፰/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የአንዱስትሪ ቀጠና ሥርዓት አፈፃፀምን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ስድስት

## የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት

### ፲፭. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

፩/ በቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘኖች ሥርዓት መጠቀም የሚችሉት ምርታቸውን ሙሉ በሙሉ ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡ፣ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው እና በኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የሚወጣውን መስፈርት የሚያሟሉ የማምረቻ መጋዘኖች ያሏቸው አምራቾች ይሆናሉ፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችለውን የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጠቃሚዎቹ የማምረቻ መጋዘኖች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ፡፡



b) present to the Ethiopian Revenues and Customs Authority, evidence that shows the commodities destined for export have been exported within one month from the date of leaving the industrial zone.

5/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall charge duty on commodities destined for local consumption on the basis of all industry rates before such commodities leave the industrial zone.

6/ Where a beneficiary of the industrial zone scheme applies for extension of the period stipulated under sub-article (3) of this Article one month before the expiry of such period, the Ethiopian Revenues and Customs Authority may, by taking into consideration the nature of the raw material, extend the period for not more than one year.

7/ A beneficiary of the industrial zone scheme who has not secured permission for extension of the period in accordance with sub-article (6) of this Article shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw material, be required to pay 50% of the duty.

8/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Ethiopian Revenues and Customs Authority may issue directive prescribing procedures for the application of the industrial zone scheme.

## PART SIX

## THE BONDED EXPORT MANUFACTURING WAREHOUSE SCHEME

### 15. Beneficiaries of the Scheme

1/ Beneficiaries of the bonded export manufacturing warehouse scheme shall be producers who, are engaged exclusively in production of export commodity, have obtained certificate of eligibility from the Ministry of Industry, and have manufacturing warehouses which meet the standards set by the Ethiopian Revenues and Customs Authority.

2/ The Ministry of Industry shall issue directive stipulating the criteria to be fulfilled to obtain certificate of eligibility to become beneficiary of the bonded export manufacturing warehouse scheme, and the Ethiopian Revenues and Customs Authority shall issue directive defining the standards to be met by the manufacturing warehouses owned by beneficiaries of the scheme.

## ፲፮. የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት አፈፃፀም

፩/ የቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ወደ አገር ያስገባው ጥሬ ዕቃ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ወደ ማምረቻ መጋዘኑ ይጓጓዛል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን የሚገባውንና ከመጋዘኑ የሚወጣውን ጥሬ ዕቃ እንዲሁም በፋብሪካው ተመርቶ ወደ ማምረቻ መጋዘኑ የሚገባውንና ከመጋዘኑ የሚወጣውን ምርት ይቆጣጠራል፡፡

፫/ ወደ ቦንድድ ኤክስፖርት ማምረቻ መጋዘን የገባ ጥሬ ዕቃ ወደመጋዘኑ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ምርት ተመርቶበት ምርቱ ለውጭ ገበያ መላክ አለበት፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የጥሬ ዕቃውን ባህሪ መሠረት በማድረግ ይህ የጊዜ ገደብ ለተጨማሪ አንድ ዓመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ እንዲራዘምለት የሚፈልግ የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ የጊዜ ገደቡ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተመለከተው የጊዜ ገደብ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፭ መሠረት ታክሱን ከፍሎ አገር ውስጥ እንዲሸጥ ያልተፈቀደለት የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን ፶ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡

፮/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቦንድድ ኤክስፖርት የማምረቻ መጋዘን ሥርዓት አፈፃፀምን የሚወስን መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

### ክፍል ሰባት

### የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት

## ፲፯. የሥርዓቱ ተጠቃሚዎች

፩/ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠ ቃሚ መሆን የሚችሉት የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የሥርዓቱ ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት የሰጣቸው እና የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የሚያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መጋዘን ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ፡፡

## 16. Procedure for the Application of Bonded Export Manufacturing Warehouse Scheme

1/ Raw materials imported by a person who is beneficiary of the bonded export manufacturing warehouse scheme shall be transported to the manufacturing warehouse under the control of customs without being subject to payment of duty.

2/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall inspect raw materials brought into and taken out of the bonded export manufacturing warehouse as well as goods produced by the factory and transferred to and taken out of the manufacturing warehouse.

3/ Raw materials transferred into a bonded export manufacturing warehouse shall be put to use in the production of export commodity and the commodity so produced shall be exported within one year of transfer of such raw materials into the manufacturing warehouse; provided, however, that the Ethiopian Revenues and Customs Authority may extend such period by one additional year taking into consideration the nature of the raw materials.

4/ A beneficiary of the bonded export manufacturing warehouse scheme desiring extension of the period stipulated in sub article (3) of this Article may submit application for extension one month before the expiry of such period.

5/ A beneficiary of the bonded export manufacturing warehouse scheme who has not secured permission for extension one month before the expiry of the period stipulated in sub-article (3) of this Article, or to sell raw materials imported under this scheme upon payment of duty chargeable on such raw materials in accordance with Article 25 of this Proclamation shall, in addition to the duty payable on the unused amount of the raw materials, be required to pay 50% of the duty.

6/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Ethiopian Revenues and Customs Authority may issue directive prescribing procedures for the application of the bonded export manufacturing warehouse scheme.

### PART SEVEN

### THE BONDED INPUT SUPPLIES WAREHOUSE SCHEME

## 17. Beneficiaries of the Scheme

1/ Beneficiaries of the bonded input supplies warehouse scheme shall be persons who have obtained certificate of eligibility from the Ministry of Industry and who have warehouses meeting the standards set by the Ethiopian Revenues and Customs Authority.

፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የምስክር ወረቀት ለማግኘት ሊሟሉ የሚገቡ መስፈርቶችን፣ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የተጠቃሚዎቹ የግብዓት አቅርቦት መጋዘኖች ሊያሟሏቸው የሚገቡ መስፈርቶችን የሚወስኑ መመሪያዎችን ያወጣሉ፡፡

**፲፰. የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት አፈፃፀም**

፩/ የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ተጠቃሚዎች ወደ አገር የሚያስገቡት ግብዓት ከቀረጥ ነፃ ሆኖ በጉምሩክ ቁጥጥር ሥር ከጉምሩክ ጣቢያዎች ወደ መጋዘኑ ይጓጓዛል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ወደ ቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን የሚገባውን እና ከመጋዘኑ የሚወጣውን ግብዓት ይቆጣጠራል፡፡

፫/ በቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓት ወደ አገር የገባ ግብዓት ወደ መጋዘን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ ለአምራች ካልተላለፈ የሥርዓቱ ተጠቃሚ በግብዓቱ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ እና በተጨማሪም የቀረጡን ፶ በመቶ እንዲከፍል ይደረጋል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን የግብዓቱን ባህሪ መሠረት በማድረግ የጊዜ ገደቡ ለተጨማሪ አንድ አመት እንዲራዘም ሊፈቅድ ይችላል፡፡

፬/ የቫውቸር ሥርዓት ተጠቃሚ የሆኑ አምራች ላኪዎችና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች በግብዓቱ ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ በቫውቸር ደብተር ላይ እንዲመዘገብ በማድረግ ከቦንድድ ግብዓት መጋዘን ግብዓቶችን መግዛት ይችላሉ፡፡

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን የቦንድድ ግብዓት አቅርቦት መጋዘን ሥርዓትን አፈጻፀም በተመለከተ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፲፱. የንግድ ድርጅት ባለቤትነት መተላለፍ**

፩/ በዚህ አዋጅ የተዘረጋው የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ድርጅቱን በማንኛውም ሁኔታ ለሌላ ወገን ሲያስተላልፍ በሥርዓቱ ተጠቅሞ ላስገባቸው ጥሬ ዕቃዎች ደጋፊ ሰነዶችን አቅርቦ የቀረጥና ታክስ ሂሳቡን ማወራረድ አለበት፡፡

2/ The Ministry of Industry shall issue directive stipulating the criteria to become beneficiary of the bonded input supplies warehouse scheme, and the Ethiopian Revenues and Customs Authority shall issue directive defining the standards to be met by the input supplies warehouses owned by beneficiaries of the scheme.

**18. Procedure for the Application of Bonded Input Supplies Warehouse Scheme**

1/ Input supplies imported by beneficiaries of the bonded input supplies warehouse scheme shall be transported from a customs post to such warehouses under the control of customs without being subject to payment of duty.

2/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall inspect input supplies brought into and taken out of bonded input supplies warehouses.

3/ If input supplies imported under the bonded input supplies warehouse scheme is not delivered to a producer within one year of being transferred into a bonded supplies input warehouse, the beneficiary shall, in addition to the duty payable on the input supplies, be required to pay 50% of the duty; provided, however, that the Ethiopian Revenues and Customs Authority may extend such period by one additional year taking into consideration the nature of the input supplies.

4/ Producer exporters and indirect producer exporters who are beneficiaries of the voucher scheme may buy inputs from a bonded input supplies warehouse by causing to be recorded on the voucher book the amount of duty payable on the inputs.

5/ Without prejudice to the provisions of this Article, the Ethiopian Revenues and Customs Authority may issue directive defining the procedure for the application of the bonded input supplies warehouse scheme.

## PART EIGHT

## MISCELLANEOUS PROVISIONS

**19. Transfer of Enterprise Ownership**

1/ A beneficiary of any of the duty incentive schemes established by this Proclamation transferring in any manner ownership of his enterprise to another person shall be required to settle accounts of duties and taxes, on the basis of supporting documents, for raw materials imported under the scheme.

፪/ ተተኪው ባለቤት የሥርዓቱ ተጠቃሚ መሆን የሚፈልግ ከሆነ ለሚመለከተው አካል አመልክቶ በዚህ አዋጅ መሰረት አዲስ የምስክር ወረቀት ማውጣት ይኖርበታል፡፡

## ፳. በአገር ውስጥ ስለሚገዙ ጥሬ ዕቃዎች

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፰(፬) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ በተፈቀዱ የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓቶች ተጠ ቃሚ የሆኑ አምራች ላኪዎችና ቀጥተኛ ያልሆኑ አምራች ላኪዎች በአገር ውስጥ በሚገዟቸው ጥሬ ዕቃዎች ላይ ቀረጥ መክፈል ይኖርባቸዋል፡፡ ሆኖም የከፈሉት ቀረጥ በተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት መሠረት እንዲመለስላቸው የመጠየቅ መብት ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተከፈለውን ቀረጥ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው የተፋጠነ ሥነ ሥርዓት መሠረት ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## ፳፩. ጥሬ ዕቃና ምርትን ስለማስተላለፍና የቀረጥ ሂሳብን ስለማወራረድ

፩/ ከቀረጥ ነጻ ሆኖ በገባ ጥሬ ዕቃ የተመረተ ሸቀጥ በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ወደ ውጭ የተላከ እንደሆነ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ይወራረዳል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆነ ጥሬ ዕቃ አቅራቢ ከቀረጥ ነፃ ያስገባውን ጥሬ ዕቃ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ ለሆነ አምራች ካስተላለፈ ጥሬ ዕቃውን በመጠቀም የተመረተን ሸቀጥ ወደ ውጭ እንደላከ ተቆጥሮ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ ሂሣብ ይወራረድለታል፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ የሆነ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ከቀረጥ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ያስገባውን ወይም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተረከበውን ጥሬ ዕቃ ተጠቅሞ ያመረተውን ምርት ጥሬ ዕቃውን በተረከበ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ፡-

ሀ) በግብዓትነት ለሚጠቀምበት ተመሣሣይ መብት ላለው ለሌላ ቀጥተኛ ያልሆነ አምራች ላኪ ወይም ለአምራች ላኪ ያስተላለፈ፤ ወይም

ለ) በሸቀጥነት ለላኪ ያስተላለፈ፤

እንደሆነ ጥሬ ዕቃውን በመጠቀም የተመረተን ሸቀጥ ወደ ውጭ እንደላከ ተቆጥሮ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው የቀረጥ ሂሣብ ይወራረድለታል፡፡

2/ A transferee intending to become beneficiary of the scheme may apply to the appropriate body to obtain a new certificate of eligibility in accordance with this Proclamation.

## 20. Raw Materials Purchased Locally

1/ Without prejudice to the provision of Article 18(4) of this Proclamation, producer exporters and indirect producer exporters who are beneficiaries of the schemes under this Proclamation shall be required to pay duty on their local purchase of raw materials; provided, however, that they shall be entitled to claim refund of the duty paid in accordance with the duty draw-back scheme.

2/ The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall refund the duty paid as provided in sub-article (1) of this Article, with summary procedure to be prescribed by the Ministry of Finance and Economic Development.

## 21. Transfer of Raw Materials and Products and Settlement of Suspense Account of Duty

1/ The account in suspense of duty payable on raw materials imported shall be settled if the commodity produced using such raw materials is exported within the time limit specified in this Proclamation.

2/ The account in suspense of duty payable on raw materials imported by a material supplier who is beneficiary of the schemes under this Proclamation shall be settled as if he exported commodities produced using such raw materials, if he transfers those raw materials to a producer enjoying similar rights under this Proclamation.

3/ The account in suspense of duty payable on raw materials imported by or delivered, pursuant to sub-article (2) of this Article, to an indirect producer exporter who is beneficiary of the schemes under this Proclamation shall be settled as if he has exported commodities produced using such raw materials, if he supplies his products, within one year from the date of receipt of the raw materials, to:

a) another indirect producer exporter or a producer exporter enjoying similar rights under this Proclamation, as input for the production of an export commodity; or

b) to an exporter as a commodity.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት ለግብዓትነት የሚውል ምርት የተላለፈለት አምራች ግብዓቱን ተጠቅሞ ያመረተውን ሸቀጥ በአንድ ዓመት ውስጥ እንደ አግባቡ ወደ ውጭ ከላከ ወይም ለላኪ ካስተላለፈ በጥሬ ዕቃው ላይ ሊከፈል የሚገባው ቀረጥ ይወራረድለታል፡፡

፭/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ምርት የተላለፈለት ላኪ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚያወጣው መመሪያ በሚወሰን የጊዜ ገደብ ውስጥ ምርቱን ወደ ውጭ የመላክ ኃላፊነት አለበት፡፡

፮/ በዚህ አንቀጽ መሠረት ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት የተላለፈለት ሰው በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ኃላፊነቱን ካልተወጣ በስተቀር አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ቀረጡን ከነቅጣቱ ይከፍላል፡፡

፯/ በዚህ አንቀጽ መሠረት የቀረጥ ሂሳብ የሚወራረድበት ሥርዓት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

## ፳፪. የግብዓት ምርት ጥመርታ እና የአጠቃላይ የኢንዱስትሪ የተመላሽ ቀረጥ መጣኔ

፩/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ይህ አዋጅ ከፀናበት ቀን ጀምሮ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የግብዓት ምርት ጥመርታን መመሪያ አውጥቶ ሥራ ላይ ያውላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው የግብዓት ምርት ጥመርታ መመሪያ ሥራ ላይ እስከሚውል ድረስ ላኪዎች ወይም አምራቾች የሚያቀርቡት የግብዓት ምርት ጥመርታ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እየታየ በሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

፫/ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የግብዓት ምርት ጥመርታ መመሪያ ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ የአጠቃላይ ኢንዱስትሪ ቀረጥ መጣኔን መመሪያ አውጥቶ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

## ፳፫. በምርት ሂደት ውስጥ ስለሚባክን ጥሬ ዕቃ

፩/ ለወጪ ንግድ ዕቃዎች ማምረቻ የዋለው ጥሬ ዕቃ ወይም ጥሬ ዕቃውን ለማምረት ጥቅም ላይ የዋለው ጥሬ ዕቃ መጠን በሚሰላበት ጊዜ በምርት ሂደት ውስጥ የባከነው ወይም የተበላሸው ግምት ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡

፪/ አምራቹ በምርት ሂደት ውስጥ በባከነው ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥ ከፍሎ የባከነውን ጥሬ ዕቃ እና ተረፈ ምርት አገር ውስጥ መሸጥ ይችላል፡፡

4/ The account in suspense of duty payable on raw materials shall be settled if a producer who received products as input pursuant to sub-article (3) of this Article, within one year, exports or supplies to an exporter, as the case may be, commodities produced using such products.

5/ An exporter to whom a product is transferred pursuant to this Article shall be responsible to export the product within a period specified by directive to be issued by the Ministry of Finance and Economic Development.

6/ A person to whom raw materials or products are transferred pursuant to this Article shall, unless he has discharged his responsibilities within the specified time limit, be liable to settle the duty including penalties stipulated under the relevant provisions of this Proclamation.

7/ The manner of settlement of accounts pursuant to this Article shall be prescribed by directive to be issued by the Ethiopian Revenues and Customs Authority.

## 22. Input and Output Coefficient and All Industry Rates

1/ The Ministry of Industry shall issue and implement directive concerning input and output coefficient, within two years from the effective date of this Proclamation.

2/ The input and output coefficient presented by producers shall, subject to review and approval by the Ministry of Industry, be used pending the issuance and implementation of the directive specified in sub-article (1) of this Article.

3/ Subsequent to the issuance and implementation of the input and output coefficient directive, the Ministry of Finance and Economic Development shall issue and implement directive concerning all industry rates.

## 23. Raw Materials Wasted in the Process of Production

1/ When calculating the amount of raw materials used in the production of export commodities, or the raw materials used to produce such raw materials, the wastage of raw materials and byproducts shall be taken into account.

2/ The producer may, against payment of duty, sell in local market, the raw materials wasted in the process of production and the byproducts.

፫/ በምርት ሂደት ጉድለት የተገኘባቸው ምርቶች ለውጭ ገበያ መላክ የማይችሉ መሆኑ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲረጋገጥ ተገቢው ቀረጥ የሚከፈልባቸው ሆኖ አገር ውስጥ ሊሸጡ ይችላሉ፡፡

## ፳፬. ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች አጠቃቀም የጊዜ ገደብ ስለማራዘም

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቀረጥ ያልተከፈለባቸው ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች በዚህ አዋጅ በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ጥቅም ላይ ውለው ለውጭ ገበያ ካልተላኩ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ካልተላለፉ የጊዜ ገደቡን ለተጨማሪ አንድ ዓመት ማራዘም የሚቻልበትን ሥርዓት የሚመለከት መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፳፭. በአገር ውስጥ ስለመሸጥ

፩/ አምራቹ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት የማምረት ወይም የመላክ ንግድ ሥራውን ያቋረጠ እንደሆነ ወይም የተረከበው ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት ለወጪ ምርት ደረጃውን ያልጠበቀ በመሆኑ ወይም ለምርት ተግባር እንዳይውል የሚከለክሉ ነገሮች ሲያጋጥሙት ወይም ምርቱ ከተላከ በኋላ ጉድለት ኖሮት ቢመለስ ለዚህም ማስረጃ ማቅረብ ከቻለ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣንን በማስፈቀድ ቀረጡን ከፍሎ ጥሬ ዕቃውን ወይም ምርቱን በአገር ውስጥ መሸጥ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተመለከተው ውጭ ቀረጥ ያልተከፈለበትን ጥሬ ዕቃ ወይም ጥሬ ዕቃውን በመጠቀም የተመረተ ምርትን በአገር ውስጥ መሸጥ የሚቻለው አግባብ ባላቸው የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ቀረጡ ከነቅጣቱ ከተከፈለ በኋላ ይሆናል፡፡

## ፳፮. ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች አጠቃቀም የጊዜ ገደብን በተደጋጋሚ አለማክበር

ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ወይም ምርቶች ተጠቅሞ ያመረተውን ምርት ወደ ውጭ ለመላክ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ መሠረት ለማስተላለፍ የተፈቀደለትን የማራዘሚያ ጊዜ ጨምሮ የተወሰነውን የጊዜ ገደብ በተከታታይ ለሦስተኛ ጊዜ ያላከበረ የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ በሥርዓቱ የመጠቀም መብቱን ያጣል፡፡

3/ Products found to be defective in the process of production may, against payment of duty, be sold in local market where it is certified by the Ministry of Industry that such products are not worthy of export.

## 24. Extending the Time Limit for Using Raw Materials and Products Subject to Duty

The Ethiopian Revenues and Customs Authority shall issue directive to prescribe procedures of extending the time limit, for one additional year, for exporting commodities produced by using raw materials or products subject to duty or for transferring them in accordance with Article 22 of this Proclamation.

## 25. Selling in Local Market

1/ If a producer who is beneficiary of the schemes under this Proclamation terminates his production or export activity because of events beyond his control, or if the raw material or product he received does not meet the required quality standard for use in the production of commodity for export or for any other reason rendering the raw material or product unusable for production, or if the exported product is re-imported because of defect, and the producer can present adequate evidence to prove same, he may, after securing the consent of the Ethiopian Revenues and Customs Authority, sell in the local market the raw materials or the product upon payment of the duty.

2/ Raw materials subject to duty or products produced by using such raw materials, except as provided for under sub-article (1) of this Article, may be sold in the local market after payment of the duty, including penalty, in accordance with the relevant provisions of this Proclamation.

## 26. Repeated Failure to Meet the Time Limit for Using Raw Materials and Products Subject to Duty

If a beneficiary of export trade duty incentive scheme successively fails for the third time to meet the time limit, including any extension thereof, for exporting products produced using raw materials or products subject to duty or for transferring them in accordance with Article 22 of this Proclamation, he shall forfeit his entitlement to the incentives scheme.

## ፳፯. ወደአገር የገባን ሸቀጥ ወይም ጥሬ ዕቃ ወደ መጣበት አገር ስለመመለስ

በወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ቀረጥ ሳይከፈልባቸው ወደ አገር ውስጥ የገቡ ጥሬ ዕቃዎችና ምርቶች በግዥ ትዕዛዙ የተመለከተውን ስፔስፊኬሽን የማያሟሉ፣ የተበላሹ፣ የጐደሉ ወይም በገበያ ተፈላጊ የሆነ ምርት ሊመረትባቸው የማይችልና ተጠቃሚው ወደ መጡበት አገር መልሶ የሚልክ ከሆነ ሳይከፈል የቀረው ቀረጥ ፭ በመቶ ይከፈልባቸዋል፡፡ በተመላሽ ቀረጥ ሥርዓት የገቡ ከሆነ ግን በተመለሰው ጥሬ ዕቃ ወይም ምርት መጠን ተሰልቶ ከተከፈለው ቀረጥ ላይ ፺፭ በመቶ ይመለሳል፡፡

## ፳፰. ወደሀገር ውስጥ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የተጣለ ገደብ

፩/ በዚህ አዋጅ በተዘረጋው የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ተጠቃሚ የሆነ ሰው ጥሬ ዕቃዎችን ከቀረጥና ታክስ ነፃ ሆኖ ወደ አገር ማስገባት ወይም በእነዚህ ጥሬ ዕቃዎች ላይ የከፈለው ቀረጥ እንዲመለስለት መጠየቅ የሚችለው ወደ አገር ከሚገባው ጥሬ ዕቃ ጋር በጥራት ተመሳሳዩ በአገር ውስጥ የማይገኝ ከሆነ ነው፡፡

፪/ የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈፃፀም ሥርዓት የሚደነግግ መመሪያ ያወጣል፡፡

## ፳፱. የወንጀል ጥፋቶችና ቅጣቶች

፩/ ማንኛውም ሰው ቀረጥ ላለመክፈል ወይም አሳንሶ እንዲከፈል ለማድረግ ስለአመራረቱ ወይም ስለሸቀጡ ዋጋ ሀሰተኛ መግለጫ የሰጠ፣ ትክክለኛ ያልሆኑ የሂሳብ መዛግብትን ወይም ደጋፊ ሰነዶችን ያቀረበ፣ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲያቀርብ ሲጠየቅ ፈቃደኛ ያልሆነ ወይም የደበቀ ወይም የዚህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎችን አፈፃፀም በማናቸውም ሁኔታ ያደናቀፈ እንደሆነ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ:-

ሀ) ጥፋቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፴ሺ እስከ ብር ፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

ለ) ጥፋቱ ለሁለተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ከስድስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፷ሺ እስከ ብር ፩፻ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፤

ሐ) ጥፋቱ ለሦስተኛ ጊዜ የተፈፀመ ሲሆን ከዘጠኝ እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፺ሺ እስከ ብር ፩፻፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ተቀጥቶ የቀረጥ ማበረታቻ መብቱ ይሰረዛል፡፡



## 27. Re-exporting Raw Materials or Commodities to the Country of Origin

Raw materials or commodities imported without payment of duty for use in the production of export commodity under the export trade duty incentives schemes which are found to be not in conformity with the purchase order specifications, damaged or which are in short delivery or which are not fit for use in the production of commodities in market demand may be re-exported to their country of origin against payment of 5% of the import duty payable on such raw materials or commodities; provided, however, that if such raw materials or commodities were imported under the duty draw-back scheme, 95% of the import duty paid on the re-exported portion of the raw materials or commodities shall be calculated and refunded.

## 28. Restriction on Importation of Raw Materials

1/ Beneficiaries of the schemes under this Proclamation shall be entitled to import raw materials free of duty or to claim duty draw-back on such raw materials if such raw materials are not available in comparable quality in local market.

2/ The Ministry of Industry shall issue directives to prescribe the procedures for the application of the provisions of sub-article (1) of this Article.

## 29. Offences and Penalties

1/ Whosoever, with intent to evade or understate the duty payable on his product, gives false information regarding the makeup or value of his products, submits inaccurate books of accounts or supporting documents, refuses to give or conceals any appropriate information when required to do so, or in any manner obstructs the implementation of this Proclamation, or regulations or directives issued hereunder shall be guilty of an offence and be punishable with:

a) rigorous imprisonment from three to five years and fine from Birr 30,000 to Birr 50,000, if the offence is committed for the first time;

b) rigorous imprisonment from six to ten years and fine from Birr 60,000 to Birr 100,000, if the offence is committed for the second time;

c) rigorous imprisonment from nine to fifteen years and fine from Birr 90,000 to Birr 150,000 with forfeiture of the duty incentives to which he is entitled, if the offence is committed for the third time.

፪/ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ከቀረጥ ነጻ ወደ አገር ያስገባውን ጥሬ ዕቃ ወይም በዚህ ጥሬ ዕቃ ያመረተውን ሸቀጥ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉት ሥርዓቶች ውጭ በአገር ውስጥ ገበያ ላይ ከሸጠ በወንጀል ጥፋተኛ ሆኖ ከሰባት እስከ አሥራ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እሥራት እና ከብር ፸ሺ እስከ ብር ፩፻፶ሺ በሚደርስ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን በአዋጅ ቁጥር ፭፻፹፯/፪ሺ አንቀጽ ፮(፲) የተሰጠው ወንጀልን የመመርመር እና በፍርድ ቤት የወንጀል ክስ የማቅረብና የመከራከር ሥልጣን በዚህ አንቀጽ ለተደነገጉት የወንጀል ጉዳዮችም ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ፴. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጐች

፩/ የተሻሻለው የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፫/፲፱፻፺፱ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የአሠራር ልማድ በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፴፩. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች

፩/ በቀድሞው የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ መሠረት ተጀምረው ይህ አዋጅ በሥራ ላይ ከመዋሉ በፊት ፍፃሜ ያላገኙ ሸቀጦችን ወደውጭ ከመላክ ሥራ ጋር በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ የተገናኙ የጥሬ ዕቃ እና የሸቀጥ አቅርቦት ግብይቶች በቀድሞው አዋጅ መሠረት ፍፃሜ ያገኛሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፪ የተደነገገው ይህ አዋጅ ከመፅናቱ በፊት ወደ አገር የገቡ ጥሬ ዕቃዎችን ወይም ጥሬ ዕቃዎቹን በመጠቀም የተመረቱ ምርቶችን ማስተላለፍን በተመለከተ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፴፪. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አዋጅ በግልጽ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ለሌሎች መንግሥታዊ አካላት የተሰጠው መመሪያ የማውጣት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ይህን አዋጅና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የወጡ ደንቦችን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

2) Whosoever sales raw materials imported free of duty in accordance with this Proclamation or commodities he produced using such raw materials, in local market, in a manner not allowed by the schemes under this Proclamation shall be guilty of an offence and be punishable with rigorous imprisonment from seven to fifteen years and fine from Birr 70,000 to Birr 150,000.

3/ The power of the Ethiopian Revenues and Customs Authority to investigate offences and to institute and follow up criminal proceedings in courts under Article 6(10) of Proclamation No.587/2008 shall also apply to offences provided for under this Article.

## 30. Repealed and Inapplicable Laws

1/ The Revised Duty Incentives Schemes Proclamation No.543/2007 is hereby repealed.

2/ No law or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with this Proclamation, be applicable with respect to matters provided for by this Proclamation.

## 31. Transitory Provisions

1/ Transactions of supplies of raw materials or commodities directly or indirectly related to export activities, occurring under the previous export duty incentives schemes proclamation and not settled prior to the entry into force of this Proclamation shall be completed in accordance with the provisions of the previous proclamation.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, the provisions of Article 22 of this Proclamation shall be applicable to the transfer of raw materials imported prior to the effective date of this Proclamation or products produced using such raw materials.

## 32. Power to Issue Regulation and Directive

1/ The Council of Ministers may issue regulations necessary for the implementation of this Proclamation.

2/ Without prejudice to the powers of other public bodies to issue directives in respect of matters specified in this Proclamation, the Ministry of Finance and Economic Development may issue directives necessary for the implementation of this Proclamation and regulations issued under sub-article (1) of this Article.

**፴፫. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፱ ቀን ፪ሺ፬ ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

**33. Effective Date**

This Proclamation shall come into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 4th day of September, 2012.**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**